ኢትዮሚዲያ

እርሰ አንቀፅ

# ኢትዮጵያ ዉስጥ አንድ ነገር እየበሰበሰ ነዉ!

## ከ17 ዓመት በኋላ ምንም የተለወጠ ነገር የለም……

***ትርጉም ፤ በአላና አብሴ***

በመጀመሪያ የወደብ በር ማጣት ነበር። መለስ የአሰብን ወደብ ምኑም ምኑም ሳይቀር አጠቃሎ ለተገንጣይ ኤርትራ አስረከቦ ኢትዮጵያን እስከ መጨረሻዉ የባህር በር አልባ አርጎ አስቀራት። ቀጥሎ ባድሜንና በሀገሪቱ በስተ ሰሜን ምስራቅ የሚገኙ አካባቢዎችም እንዲሁ ለተንገጣይ ኤርትራ ተሰጡ። ሀገሪቱ በጦር ሜዳ የተቀዳጀችውን የማያወላውል ድል ከመንጋጋዋ መንጭቆ ኢትዮጵያ በዲፕሎማቲክ መድረክ እንድትሸነፍ አመቻችቶ ባድሜን ለኤርትራ አስረከበ። መለስ ይህንን ሲያደርግ የኢትዮጵያን የባድሜን የይገባኛል ጥያቄ የሚያዳክሙ መረጃዎችን ሰብስቦ ውሉ በሚጸናበት በአለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት በመዋዋል ነዉ። ከዚያ ቀጥሎ መለስ ሶማሊያን ወረረ። ይህቺ ሃገር በእርስ በእርስ ጦርነት ዉስጥ ለረጅም ጊዜ እየማቀቀች ያለች መንግስት አልባ ሀገር ናት። ወረራዉ በአንድ አመት አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ሶማሊዎችን ከመኖሪያቸዉ አፈናቅሎ በአለም ላይ በሰዉ ልጆች ላይ እየደረሱ ባሉ ችግሮች በአስጊነቱና በአስከፊነቱ የሁለተኝነትን ደረጃ የያዘዉን ያለዉ ሁኔታም የሚያመለክተዉ መለስ መሬት ቆርሶ መስጠቱን ስራዬ ብሎ እንደተያያዘዉ ነዉ። በቅርቡ ታች አርማጭሆን፤ ቋራን፤ ተስፋ አስቆራጭ ችግር ፈጠረ። አሁን እየታየ መተማንና አብደሪስን ለዳርፉሩ ነብሰ በላ ለኦማር አልበሺር እንደ ገፀ በረከት አበርክቷል።




ኢትዮጵያውያን ያለምንም ጥርጥር በቅጥረኞች አገዛዝ ስር ወድቀዋል። ችግሩ ይህ ሆኖ ሳለ ምሁራኖች ይህንን ወለል ያለ ሀቅ ወዲያና ወዲህ ሲፈለሰፉበት ምስቅልቅሉን አወጡት። ለምሳሌ በጎአሳቢ ከሆኑ ሃገር ወዳጆች መጣጥፍ ቀንጭብ ብናደርግ፤ አንዳንዶቹ መለስ በአብዮታዊ አመለካከቶች የተተበተበ ሌኒንስት ነዉ ይሉታል። ዲሞክራት፤ ዳግሚዊ ወይም አምባገነን በማለት ኃይለ ስላሴና መንግስቱ ባሉበት ቅርጫት ዉስጥ መለስን ይደባልቁታል። (ጎልቶ አይላ) ሌሎችንም ጨምሮ ገዠዉን ክፍል የትግራይ አናሳ መንግስት ይሉታል ( ገነት መርሻ) እነዚህ አሳሳች ድምዳሚዎች ናቸዉ ምክንያቱም መለስና የቅርብ ግብረአባሮች ኮሚኒስትም ዲክታተርም አይደለም። እነሱ በኢትዮጵያ ላይ ጥልቅ የሆነ ጥላቻ ያላቸዉ ይህንን እኩይ አላማቸውን ለማፋጠን በመጀመሪያ ያስፈጸሙ በትግራ ነፃ አዉጭ ግንባር ዉስጥ ሰርገዉ ገብተው የኤርትራን የመገንጠል አላማአስፈጸሙ። በለስ ቀንቷቸዉም በኢትዮጵያ የስልጣን ወንበር ላይ ቂጢጥ ያሉ ቅጥረኞች ናቸዉ። ፎቶዉ በቀኝ በኩል የሱዳን አልበሺርን ያሳያል በስተግራ ደግሞ 1600 ኪ.ሜ ለሱዳን የሰጠዉን መለስ ዜናዊን ያሳያል
በመለስ ዜናዊ ችሮታ የሱዳን ወታደሮች በርካታ የእርሻ መንደሮችን በእሳት አጋይተዋል። ብዙ የአካባቢው ሰፋሪ ሰራተኞችን ወደ ሱዳን አስረው ወስደዋል።

“ስለ እግዚአብሔር - መለስ ኢትዮጵያን ምን እያደረጋት እንደሆነ ሊያስረዳን የሚችል አለ ?”

## አንድ ነገር እጅግ በጣም እየበሰበሰ ነዉ…

በሀምሌት ሼክስፒር በህያው መስመሩ እንዲህ ሲል ፃፈ ”በዴንማርክ ዉስጥ አንድ ነገር እየሰበሰበ ነዉ” ከጥቂት ወራቶች በፊት የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት H.R 2003 ሲያሳልፍ መለስና ግብረ በሎቹ የሃገሪቱ ሉአላዊነት ተነካ ብለዉ የአዞ እንባቸዉን አፈሰሱ። መለስ የውጫሌን ዉል ከተቀበረበት ፈልፍሎ አዉጥቶ ሚኒሊክ የኢትዮጵያን ግዛት ለጣሊያን አሳልፎ ሰጥቷል በማለትም በሚኒሊክ አፌዘበት። ” በመቀጠልም ኢትዮጵያ በምንም መልኩ ከአሜሪካ መናገሻ ከተማ የምትመራ የባናና ሪፓፐሊክ ልትሆን ኣትችልም ሲል ቃል ገባ” በኣሜሪካ የመለስ ኣምባሳድር ሳሙኤል አሰፋም የአሜሪካ ምክር ቤት” ነፃነቷን ለረጅም ጊዜ ጠብቃ በኖረች ነፃ ሃገር ዉስጥ ጣልቃ ገባ” ብሎ እሪታዉን አቀለጠዉ። የመለስ አማካሪ በረከት ስምኦንም “ይህቺ ለዉጪ ኃይል ያላጎበደደች ሉአላዊ ሀገር ናት” በማለት የምክር ቤቱን ዉሳኔ በመቃወም በአለም አቀፍ የዜና አዉታሮች ሲያጓራ ከረመ። ዛሬ መለስና ግብረ በሎቹ ገንዘብ ላለዉ በሙሉ የኢትዮጵያን ግዛቶች በማጫረት ላይ ናቸዉ። በጣም የገማ የገለማ ሀፍረተ ቢስ ተግባር እየፈጸሙ ነው።

## የመለስ የማምታታት ዘመቻ

መለስ ያቀነባበረዉ አሳፋሪዉን ምርጫ እንዳገባደደ ለማምታቻ የፈጠረዉ ግርግር አስገርሞናል። በከፍተኛ ወጭ የአፍሪካን የአትሌቲክስ ዉድድር በአዲስ አበባ ስፓንሰር አድርጓል። “9 ሚሊዩን ዜጎች በሀገሪቱ እየተራቡ ነዉ” በሀገሪቱ ምንም ችግር እንደሌለ ለማሰመሰል የታቀደ ነዉ።

አሁን ስንሰማ ለአለፉት አራት አመታት ከሱዳን ጋር ሲደራደርባቸዉ የቆየባቸዉ ድርድሮች ለመለስ ፍሬ እያፈሩለት ለሀገሪቱ ግን እሬት እያበቀሉ ናቸዉ። የሱዳኑ አልበሺር ለመለስና የጥቅም ተካፋዩቹ ድጋፍ እስከሰጡ ድረስ እነመለስ ስልጣናቸዉ ሳይነካ ይቆያሉ። ለዚህ ዉለታ መክፈያ ደግሞ የፈለገዉን የኢትዮጵያን ድንበር ቆርሶ በአነስተኛ ክፍያ መዉሰድ ይቻላል። የመለስ የማምታታት ዘመቻ በእኛ ላይ የሚፈጥረዉ ብዥታ የለም። የመለስ ለዳርፋሩ ነብሰ በላ ለአል በሺር መሬታችንን አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ አሌ የማይባል ትኩረታችንን በጣም የሳበ ጉዳይ ነዉ። መረጃዎቻችንንም እንደሚከተለዉ እናቀርባለን።

ለአለፉት ብዙ አመታት ከወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ጽፈት ቤት እየሾለኩ የሚወጡት ብዙ መረጃዎች ከሱዳን ጋር የድንበር ክልል ለመዋሰን መንግስት ድርድር

ላይ እንደነበር ይጠቁማል። በቅርቡም የሱዳንና የኢትዮጵያ ወሰኖችን የሚለዩ ችካሎች ቆመዋል ይባላል። የታች አርማጭሆና የአካባቢዉ ነዋሪም አዋሳኝ ችካሎቹን በእምቢተኝነት በመነቃቀሉ መለስ በደንቀሮ ጀሌዎቹ የበቀል እርምጃ በነዋሪዉ ላይ ወስደዋል። በታች አርማጭሆና በአካባቢዉ ያሉ አዋሳኝ የኢትዮጵያ ከተሞች ከቅርብ ቀናት ወዲህ በሱዳን የጦር ኃይል ቁጥጥር ስር ናቸዉ።

በርካታ ገበሬዎች እርሻቸዉና የእርሻ መሳሪያቸዉ ተወስዶባቸዋል። የጀርመንና የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያዎች የተሰራዉን ደባ እና በአካባቢዉ ላይ የሱዳን ወታደሮች የመስፈራቸዉን እዉነትነት ለማረጋገጥ ከአካበቢዉ ህዝብ ጋር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ አሰምተዋል። አንድ የአካባቢዉ የወያኔ ባለስልጣን በተዘዋዋሪ ለአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ እንዳረጋገጠዉ የድንበር ከተሞችን ለሱዳን ለመስጠት እቅድ እንዳለና ሱዳንም ለኢትዮጵያ የምትሰጠዉ በግልፅ ይህ ነዉ ተብሎ የተገለጸ ነገር ኣለመኖሩን ገልጿል።

የአካበቢዉ ነዋሪዎች የሚኖሩበት ስፍራ የሱዳን መሆኑን ማረጋገጫ እንዲፈርሙ መገደዳቸዉንና አንፈርምም ያሉት ተከሰዉ ወደ ሱዳን ፍ/ቤት ለመወሰዳቸዉ በቂ አስተማማኝ መረጃዎች አሉ። በታች አርማጭሆ በኩል ያለዉን ለሙን መሬት የኢትዮጵያ መንግስት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን አስመልክቶ መለስ ዜናዊ በተለያዩ ወገኖች ማብራሪያ እንዲሰጥበት ተጠይቆ በጉዳዩ ላይ ምንም የሰጠዉ አስተያየት የለም። ከላይ በተዘረዘሩት መረጃዎች በመነሳት በጉዳዩ ላይ የሚከተሉትን ትንታኔዎች አቅርበናል።

## የመለስ የታች አርማጭሆንና አዋሳኝ የድንበር ከተሞችን ስለመሸጥ

መለስ ታች አርማጭሆን እንደ ግል መሬቱ ለመሸጡ ምንም ጥርጥር የለንም። እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረስነዉ ከዚህ ዉጪ ምንም አሳማኝ ምክንያት ስላጠንበትና የአለም አቀፍ የድንበር አወሳሰን ሕግና ደንብ ጠበብቶችም ጉዳዩ በምንም መልኩ ያለም አቀፍ ሕጎችን ያልተከተለ ሂደት መሆኑን ስለአስገነዘቡን ነዉ። በሙያዉ የተካኑት የሕግ አማካሪዎቻችን እንደሚሉት አንድ ሃገር ግዛቱን ለሌላዉ ሃገር አሳልፎ ሲሰጥ በይፋ የሚታወቀዉ አሰራር የማዘዋወር ዉሎች ይባላሉ።

እነዚህም ዉሎች ረቂቅና ዉስብስብ የሆኑ ሰነዶች ላይ ዉሳኔ ይሰጣሉ። ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጡባቸዉ ጉዳዮችም ዉስጥ የድንበሩን መስመር አመልካች የኬንትሮስ (Latitude) እና የኬክሮስ (Longitude ) ቁጥሮች፤ የሚካለለዉን ግዛት ዉዲያዉኑ የመዉሰድ መብትና በተካላይ ቦታ ላይ ያሉ ነዋሪዎች የካሳ መብት፤ በቦታዉ ላይ ያሉ ወታደሮችን ከቦታዉ የማንሳት መብት፤ ሕጋዊ ሰነዶችንና መዝገቦችን ማዛወር በተጨማሪም ዉሉ ግዛቱን ወደ ሌላዉ የሚያዛዉረዉ ሃገር የሚያገኘዉን የገንዘብም ይሁን የሌላ ጥቅሞችን ያካትታል። በዚህ መሰረት እንደተገለፀልን ለምሳሌ ታች እርማጭሆና አዋሳኝ ከተሞች የአለም አቀፍ ሕጎችን በጠበቀ ሁኔታ በአግባቡ ወደ

ሱዳን የሚዛወሩ ከሆነ ዝዉዉር የሚፈፀመዉ ቀደም ብለን በዘርዘርናቸዉ ውሎች መሰረት "የታች አርማጭሆና የአዋሳኝ ከተሞችን ዉል በመዋዋል ነዉ።" ይህንን አስምልክቶ መለስ ለሕዝብ ያሳወቀዉ ነገር የለም። በጉዳዩ ላይ ሕዝቡ በፍፁም አልተወያየበትም። በመለስም ሆነ በአልበሺር በጉዳዩ ላይ ሰፊ መግለጫ አለመስጠቱ፤ ዉሉ በአልበሽርና በመለስ መካከል የተደረገ "በሚስጥር የተያዘ ዉል" መሆኑን ያሳያል። ይህ ውል የሚጸናው ሁለቱ ኣባገነን ባለስልታናት እስከቆዩ ድረስ ብቻ ነው። የሕግ አማካሪዎቻችን እንደሚሉት የዚህ አይነት ስምምንት ሁለት ታላላቅ ችግሮች ይኖሩታል። አንደኛዉ ማንኛዉም በሚስጥር የተደረገ ዉል በኢትዮጵያ ሕገመንግስት መሰረት ሕጋዊነት የለዉም። "<u>መለስ የኢትዮጵያን ግዛቶች በሚስጥር ለሱዳን ማዛወር ማለት አንድ ሌባ የዘረፈዉን ንብረት ለሌላ ሌባ በሕጋዊነት ማስተላለፍ ማለት ያህል</u> ነዉ።" የመለስ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር ቢሆንም በጉዱዩ ላይ ብቻዉን መወሰን አይችልም። ከስልጣኑ በላይ ነው። ሁለተኛ ማንኛዉም በሁለት አምባገነኖች መካከል በሚስጥር የተደረገ የድንበር ስምምነት የሚፀናዉ እነሱ በስልጣን እስካሉ ብቻ ነዉ። ቀጥሎ የሚመጣዉ የኢትዮጵያ መንግስት ለዉሉ ተገዥ ለመሆን ሕጋዊ ግዴታ የለበትም።

## በአለም አቀፍ ሕግ መሰረት የሚደረግ ህጋዊ የመሬት ኣሰጣጥ

የሕግ ባለሙያዎች እንደሚያስረዱን ሃገሮች ግዛታቸዉን ከኋላ ኪስ መዘዉ ለሌላዉ አይሰጡም። በጦርነት ተሸንፈዉ ካልሆነ ሃገሮች ሁልጊዜ ግዛቶቻቸዉን የሚለቁት አንድም በአለም አቀፍ ፍ/ቤት ተወስኖባቸዉ ወይም ደግሞ በሽምግልና በተደረጉ ድርድሮች መሰረት ነው። ለምሳሌ 100 000 ሰዎች ተሰውተው ኢትዮጵያ የማያወላዉል ድል በወራሪዉ ላይ ከተቀዳጀች በኋላ መለስ ባድሜን ለኤርትራ አስረክቧል (ይህ ማለት መለሰ ባድሜን ለሚወዳት ኤርትራ በደስታ አይሰጥም ለማለት አይደለም። ታች አርማጭሆንም እንዲሁ።)

አንዳንድ ጊዜ የመሬቱን ዋጋና የመሬቱን ይገባኛል ጥያቄ ሊያስከትል የሚችለዉን ችግር በማመዛዘን አንድ ሃገር መሬቱን ይገባኛል ለሚለዉ ወገን ይመልሳል። በ1978 እስራኤል ከግብፅ ጋር የሰላም ዉል ስትፈርም በሁለቱ ሃገራት መካከል ወደፊት ጦርነት እንዳይነሳ በሚል የሲናይን የባህር በር ለግብፅ መልሳለች። በሌላ በኩል አንድ ሃገር የፓለቲካና የኢኮኖሚ አላማዉን ለመሰረዝ ወይም ለመሻር ግዛቱን ለሌላዉ ያዛወራል። በ1997 እንግሊዝ የሆንግ ኮንግ ግዛቷን ለቻይና ስጥታለች። ይህም እንግሊዝ ከቻይና ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከርና ለሆንግ ኮንጎችም አስተማማኝ የኢኮኖሚና የፓለቲካ ነፃነት ለመፍጠር ነዉ። የታች አርማጭሆን መሬት ለሱዳን የሚያሰጥ ምንም ተገቢ ምክንያት የለም። በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል የወሰን ግጭት ተፈጥሮ ለእርቅ ድርድር ችሎት ሲደረግ አላየንም። በየትኛዉም የሱዳን መንግስት የአርማጭሆን መሬት የይገባኛል ክስ በአለም አቀፍም ሆነ በሌላ ችሎት አቤቱታ አላቀረበም። ለተባበሩት መንግስታትም ሆነ ለተመሳሳይ ድርጅት በጉዳዩ ላይ እርምጃ እንዲወሰዱ ሱዳን ያቀረባቸዉ ጥያቄ የለም ።

ሁለቱ ሃገሮች እየተዋጉ አይደለም። ጦርነትን የሚያስከትል የመጠላላት መንፈስ በሁለቱም ሃገሮች ላይ አይታይም። የተባሉት የድንበር ከተሞችን በመስጠት ኢትዮጵያ የምታገኘዉ ጥቅም አልተገለፀም። የድንበር ከተሞቹ በሚስጥር ለሱዳን አሳልፎ መስጠትን የሚደግፍ አንድም እንኳን ምክንያት ይገኛልን? አንድም ምክንያት ፈልገን አላገኘነም። ስለዚህ መለስ እራሱንና ብጤዎቹ ወሮበላ ጓደኞቹን በገንዘብ ለማንበሽበሽ ከበሺር ጋር ተዋውሏል የሚለዉ ድምዳሜ ላይ ደርሰናል።

## የሱዳኖች የታች አርማጭሆና የድንበሩ አካባቢ የይመለስልኝ ጥያቄ

በእኛ እምነት የሱዳኖች ጥያቄ የታች አርማጭሆን አካባቢዉ የቀድሞ ግዛታችን ነዉና ለኛ ይገባል የሚል ነዉ። (naked land grab) ለሙን የኢትዮጵያ መሬት ከሕግ ዉጪ ለመዉሰድ በእኛ እምነት የሱዳን የይገባኛል ጥያቄ የተመሰረተዉ ምንም ታሪካዊ ማስረጃ በሌላቸዉ አመለካከቶችና ሱዳን በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር በምትተዳደርበት ጊዜ በተሰመረ የድንበር መሰመር ነዉ። ያም ሆነ ይህ ሀቁ የታች አርማጭሆን የድንበር አካባቢዎቹ ተዋስናዋል።? ከሚኒሊክ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂዎች እንደ ግዛታቸዉ ጠረፉን ከወራሪዎች ተከላክለዋል፤ የእንግሊዝ ካርታ ተብዩውም ዝም ብሎ በአንድ ወገን የተዘጋጀና በርካታ ስህተቶችን የያዘ ነዉ። ኢትዮጵያ ማድረግ ያለባት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚያስከብርላትና የሕዝባቿን ደህንነትና እድገት የማይፃረር አለም አቀፍሕጎችን ማክበር ነዉ።በአካበቢዉ ተወለደዉ ያደጉ፤ የአካበቢዉን ታሪክና ደንብ ጠንቅቀዉ ያወቁ 80ና በ90 እድሜ ላይ ያሉ አዛዉንቶች በድንባሩ ዙሪያ የተነሱ ጉዳዮችን የሱዳንን የመሬት ይገባኛል ጥያቄ መሰረት ቢስ ነዉ ይላሉ። በጉዳዩ ጥልቅ እዉቀት ያላቸዉና ድንበሩን ያጠኑት የድንበር ኮሚቴ መረጃዎችን የሚመረምሩ አባላት የተለያዩ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ እንደሚሊት እዲያውም የኢትዮጵያ ደንበር ከአሁኑ ደንበር ወደ ሱዳን ግዛት ውስጥ ገባ ብሎ ነዉ በመረጃዎቻቸዉ እንዳሳዩት መሬት መስጠት ያለበት ሱዳን እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም።

## ግዛትን ከህገ መንግስት ውጭ አሳልፎ መስጠት

አርማጭሆንም ሆነ ሌላዉን የኢትዮጵያን ወሰን ለሱዳን ለመስጠት መለስ ምንም ሕገ መንግስታዊ ስልጣን የለዉም። “ኢትዮጵያ የምትከተለዉ የዉጭ ግንኙነት መመሪያ” የሚያካትተዉ አንቀፅ 86 እንደሚፈቅደዉ’ “ኢትዮጵያ የምትከተለዉ የዉጭ ፓሊሲ በእኩልነት በጋራ ጥቅሞች ላይ የተመሰረተና ሀገሪቷ የምትዋዋላቸዉ አለም አቀፋዊ ዉሎች ሁሉ የሀገራቱን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ነዉ።” አንቀፅ 74 ጠቅላይ ሚኒስትሩ “የሃገሪቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴና በመንግስት እየተደረጉ ስላሉ ጉዳዮችና እና የወደፊት እቅድን በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባዎችን ለሕዝብ ተመራጮች ምክር ቤትያቀርባል” እንዲሁም “ጠ/ሚኒስትሩ ሕገ መንግስቱን የመጠበቅና ለሕገ መንግስቱም መገዛት አለበት”

- ኢትዮጵያ የድንበሩን አካባቢ ለሱዳን በመስጠት የምታገኘዉ ጥቅም ምንድን ነዉ?

- የነዚህ ቦታዎች ለሱዳን መሰጠት 'የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ጥቅም በምን በልኩ ያስጠብቃል?
- መረቱን መስጠቱ 'የኢትዮጵያን ሉአላዊነት እንደት ያሰረክባልከብረዋል'
- መለስ ከአልብሽር ጋርይትዋዋለውን ይሚስጢር ውል ልምን ብይፋ ኣላድረገውም?

## ዝምታ አበዛን....

የአሜሪካ ምክር ቤት በኢትዮጵያ ያለውን የሰበአዊ መብት ይዞታ አስመልክቶ ውሳኔ ሲያሳልፍ አስመሳዮቹና ትእቢተኞቹ የኢትዮጵያ ልእልና ተሟጋቾች ነን ባዮች በሉአላዊነት መከበር ስም ሲቧርቁ ምንም ኣላልንም። መለስ የሀገራችን ክፍል በዘዴ አሳልፎ ለጠላት ሲሰጥ ጆሮ ዳባ ልበስ አይነት ዝም አልን።ነገር ግን ለዝምታ የሚከፈል ከፍተኛ ዋጋ አለ።

ፓስተር ኒሙለር ለጀርመን ዜጎች በተለይም ለምሁሩ ካስተላለፉቸዉ መልእክቶች እንግር። "ናዚ ስልጣኑን ሲቆናጠጥ በመጀመሪያ ናዚዎችን፤ ኮምኒስቶችን ለማጥቃት መጡ። ኮሚኒስት ስላልነበርኩ ዝም አልኩ። ቀጥሎ የሰራተኛ ማህበሩን ሊያጠፉ መጡ፤ የሰራተኛዉ ማህበር አባል ስላልነበርኩ በዝምታ ተመለከትኩ። ቀጥሎም ይሁዶችን ሊያጠፉ መጡ ይሁዳዊ ስላልሆንኩኝ ዝም አልኩኝ፤ ቀጥሎም ወደ እኔ መጡብኝ ሁሉን ጨርሰዉ እኔ ሲደርሱ ተዉ ባይ ሰዉ አልነበረም ሁሉም አልቀዋል።"

መለስና ወንጀለኛ ግብረ አባሮቹ ስልጣን ይዘዉ ' ታማኝነታችን ለኤርትር ነዉ ኤርትራንም እስከመጨረሻዉ እንከላከላለን' ሲሉን የሰማነዉን ማመን አቅቶን በዝምታ ተዋጥን፤ ሀገራችን የባሕር በር አልባ መሆኗን አረጋገጡ፤ ባድሜ ለኤርትራ ስትሰጥ የትግራይ ተወላጅ ሳላልሆን ዝም አልን። መለስ ኦሮሞዎችን ሲጨፈጭፍ ኦሮሞ ስላልሆን ፀጥ አልን፤ አፋሮች ጠቅላላዉ የቀይ ባሕር ዳርቻ የኢትዮጵያ ዋና አካል ነዉ በማለታቸዉ መንደራቸዉ በአውሮፕላን እና በመደበኛ ጦር ሲጠቃ ምንም አልተናገርንም፤ ምክንያቱም አፋሮች ስላልሆን፤ መለስ በመቶ የሚቆጠሩ ጋምቤላዎችን ሲገድል ዝም አልን ምክንያቱም አኙዋክ ስላልሆን የቅንጅትን ደጋፊዎችን ሲጨፈጭፍና መሪዎቹን ሲያስር ቅንጅት ስላልሆን ዝም አልን። ዛሬ ደግሞ መለስ 1600 ኪ.ሚ ርዝመት ያለዉን መሬታችንን ለባእድ ሲሰጥ በፈፁም ዝም ማለት የለብንም። ምርጫችን እንደገና ዝምታ ከሆነ ብዙም ሳይቆይ ኢትዮጵያም ኢትዮጵያዊነትም አይኖሩም።

መለስ የኢትዮጵያን መሬት ለኤርትራና ለሱዳን ብቻ በሀራጅ መሸጥ ብቻ ሳይሆን አባይንም ለግብፆች ሸጧል ብለን እናምናለን። እያንዳንዱን መሬታችን ስንዝር በስንዝር ሸጦ ሳይጨርስ እፎይ አይልም ኃይላችንን አስተባብረን በቃ ማለት መቻል አለብን በጋራ ጉየዳዮቻችን ላይ አብረን ለመስራት የሚያቀራርበንን ድልድይ አብረን

እንድንገባ በድጋሚ እንጠራለን። ማንኛውም በኢትዮጵያ ዉስጥ ያለ ብሔረሰብና የፓለቲካ ድርጅቶች በህብረት እነዚህን ቅጥረኞች ጠራርገን ከሀገራችን ማስወጣት አለብን።

መለስ ኢትዮጵያ የማንም አይደለችም፤ ልሸጣት ልለዉጣት ለማንም ልሰጣት ቢያሻኝ ለፈለኩት ብሰጣት ከልካይ የለብኝም የሚል አስተሳሰብ አለዉ። በእኛ እምነት ኢትዮጵያ የኢትዮጵያኖች ናት፤ እምቢ አሻፈረኝ ብለን አብረን ካልጮህን በእርግጥም የቅጥረኞች መፈንጫ ሜዳ ትሆናለች፤ ጥያቄ ለሁላችንም ግልፅ ነዉ. መለስ ሀገርን ማፈራረሱን ሲቀጥል እኛ የሀገር ግንባታዉን ማካሄድ የለብንም?

*ከአዘጋጁ.በጽሁፋችን ዉስጥ የተጠቀሱትን ቴክኒካል ጉዳዮች በተመለከተ ማብራሪየ ለሰጡ የሕግ ባለሙያዎች ምስጋናችንን እናቀርባለን።*

**ማሳሰቢያ** ይህ ጽሁፍ በኢትዮሚዲያ የውጣው በሚያዝያ 27 ቀን 2000 Something is rotten in the state of Ethiopia የሚለው ጽሁፍ ትርጉም ነው